# አፈዳቪት እያልኩ ሁለገብ መረጡ

የስልጣን ጥም መጥፎ አጓጉል አባዜ
አዛውንት አኖህላይ ከቶ ማይመርጥ ጊዜ
ተበላሁ ቀደሙኝ ጋዜጣ ላይ ወጡ
ስማቸው ተጠራ ዝናን አተረፉ
ባዶዬን ቀረሁኝ መድረኩም ራቀኝ
ስሜን የሚጠራ አንድም ሰው ሳይገኝ
ስንት ዓመት ልባክን ስንት ዘመን ልታገል
ለስልጣን ካልበቃሁ ተክለ ሰቤን ሳልተክል
ትግል መራራ ነው ትግል ረጅም ነው
እልህን አስጨራሽ መራራ ክፉ ነው
እያሉ አደከሙን አቋራጭ መንገዱን ዘግተውት ጭራሹን::
ሰባ ዓመት ደረስኩኝ የከርታታ ኑሮ
ኢንጂኔር ዶክተሩ እያየሁ ሲዝናና እገሌ ተብሎ
ታዲያ ምን ፈርዶብኝ በስደት ልቆላ
ጎንበስ ደፋ ብሎ እያለ ሚበላ?
ደረቅ ችኮ ቡድን መርህ አክራሪዎች
ሊቀመንበር እምቢ ሁሌም ትግል ባዮች
ታዲያ በምን ዕዳ በስደት ልጠበስ
ፈርሜ አፊዳቪት ውርደትን ዋጥ አርጎ ልሞላ ስችል ከርስ::
በጥባጩ በዛና የምጥ ልጅ አንጃዬን በአጭር የሚያስቀሩ
አፊዳቪት እያልኩ ሁለገብ መረጡ
36ኡ ትላንትን ረስተው በአጓጉል ሲጓዙ
ወዴት ሽርተት ብዬ ሁለገብ ቀረርቶን ዘመርኩ እንደነሱ::
ጊዜ መግዛት ብልሀት አመራሩ የእኔ
ሰላም ትግል ብሎ አፊዳቪት አቅፎ ይሄዳል ፍንፍኔ::
ተንኮሌ ያልገባው የሞኝ አንጃ መንጋ
ትግል እርም ማለቴን መረዳት ያቃተው በቁሙ የተኛ
ዋይ ዋይ ቢል ቢጮህም ሰሚ አያገኝም
የስልጣን ጥም መጥፎ ከትግል አይሰምርም
የደቀቀ አዛውንት ከጎበጠ ኋላ መቸም ቀና አይልም::

ግርማ ዋሲሁን